# አስቸኳይ ትኩረት የሚሹ ሀገራዊ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች

መጋቢት 13/2014

## የኦሮሚያ እና የአማራ ክልል ሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ፡

በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን በተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ሰዎች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታስረው የነበሩ ቢሆንም እስካሁን ፍርድ ቤት ሳየቀርቡ በእስር እንደሚገኙ፤ በምስራቅ ወለጋ ጉቶ ጊዳ ወረዳ የተለያዩ መኪናዎችን በማስቆም ዘረፋዎች በተደጋጋሚ እየተፈጸሙ እንደሚገኙ እና በአካባቢው ያለውን የጸጥታ ሁኔታ በመስጋት ብዙዎች ከአካባቢው በመፈናቀል ላይ መሆናቸውን ኢሰመጉ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በተለያዩ ወረዳዎችና ቀበሌዎች በተደጋጋሚ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ሲፈጸሙ ቆይተዋል፡፡ ይህንንም ኢሰመጉ በተለያዩ መግለጫዎች ሲያሳስብ ቆይቷል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በ09/07/2014 ዓ.ም አርብ ቀን ከ ለሊቱ 6 ሰአት ላይ አምቦ ወረዳ ኢላም ቀበሌ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ቄስ አምደጺዮን የማነ ገ/ማሪያም የተባሉ የ55 ዓመት አዛውንት እና አቶ ተፈራ ሀይሉ የተባሉ የ100 ዓመት እድሜ ባለጸጋ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በአሰቃቂ ሁኔታ በሸኔ ታጣቂዎች መገደላቸውን ኢሰመጉ በአካባቢው ከሚገኙ የመረጃ ምንጮች ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

በምስራቅ ሸዋ ዞን ፈንታሌ ወረዳ አላጌ ቀበሌ ውስጥ ልዩ ቦታው መርቲ ፋብሪካ አካባቢ በ09/07/2014 ዓ.ም ከምሽቱ 2 ሰአት አካባቢ ማንነታቸው ባልታወቁ ታጣቂዎች በተፈጸመ ጥቃት በርካታ ወጣቶች የተገደሉ ሲሆን ብዙ ወጣቶችም ጉዳት ደርሶባቸው በሆስፒታል ውስጥ የህክምና ክትትል እየተደረገላቸው እንደሚገኝ ኢሰመጉ ከደረሰው መረጃ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

## የቤንሻንጉል ጉሙዝ እና የደቡብ ክልል ሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ፡

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተለያዩ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች እየተፈጸሙ ያሉ ግድያዎች፣ የአካል ጉዳት፣ ማፈናቀልና ንብረት ማውደም አሁንም ተባብሶ መቀጠሉ ኢሰመጉን በከፍተኛ ደረጃ ያሳስበዋል፡፡

በደቡብ ክልል ጉራፈርዳ ወረዳ ልዩ ስሙ አርጌ ብርሀን በተባለ ቦታ አንድነት ፈቃዱ የተባለ የ18 አመት ወጣት በ30/06/2014 ዓ.ም በአሰቃቂ ሁኔታ ማንነታቸው ባልታወቁ ቡድኖች መገደሉን፤ በቁጫ ወረዳ፣ በቁጫ አልፋ ወረዳ እና በሰላም በር ከተማ በ08/07/2014 ዓ.ም በርካታ ሰዎች በፖሊስ ድብደባ የተፈጸመባቸው እንደሆነ፤ በቁጫ ወረዳ ጋሌ ሞንላ ከተማ በሞንላ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ 15 ሰዎች ታስረው እንደሚገኙ እና በአጠቃላይ በቁጫ ወረዳ በተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ በርካታ ሰዎች ከህግ ውጪ በእስር ላይ እንዳሉ ኢሰመጉ ባገኛቸው መረጃዎ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡ በተመሳሳይ በደቡብ ክልል ጋሞ ዞን ቁጫ ወረዳ በተለያዩ ቀበሌዎች ሲፈጸሙ የነበሩ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ኢሰመጉ ሲከተተል እና በጉዳዩ ዙሪያ መግለጫዎችን ከተለያዩ ምክረ ሀሳቦች ጋር ሲያወጣ ቆይቷል አሁንም በማውጣት ላይ ይገኛል፡፡

በደቡብ ክልል በአማሮ ልዩ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች በሚኖሩ ነዋሪዎች ላይ የሸኔ ታጣቂዎች በተለያዩ ጊዜያቶች በሚፈጽሙት ጥቃት በርካታ ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል፣ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፡፡ ኢሰመጉ በአማሮ ወረዳ አይደረሰ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በቅርበት ሲከታተል የቆየ ሲሆን በተለያዩ ጊዜዎች መግለጫዎችን በማወውጣት መንግሰትን ሲያሳስብ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን በአካባቢው ያለው ችግር አሁን ተባብሶ የቀጠለ ሲሆን ከዲላ ወደ አማሮ የሚወስደው መንገድ ከተዘጋ ከወር በላይ እነደ ሆነው እና ከቡሌ ሆራ ወደ አማሮ ኬሌ የሚወሰደው መንገድም በቅርቡ በሸኔ ታጣቂዎች መዘጋቱን ኢሰመጉ ካገኛቸው መረጃዎች ማረገገጥ ችሏል፡፡

በተጨማሪም በደቡብ ክልል ኮንሶ ዞን አማሮ ልዩ ወረዳ፣ ቡርጂ ልዩ ወረዳ፣ አሌ ልዩ ወረዳና የቀድሞ የጉማይዴ ወረዳዎች ላይ ግድያ፣ የአካል ጉዳት፣ ንብረት ውድመት፣ ማፈናቀል እና ሌሎችም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሲፈጸሙ ቆይተዋል፡፡ ይህንንም ተከትሎ ኢሰመጉ የምርመራ ስራዎችን በመስራት በግኝቶቹ ዙሪያ መግለጫዎችን መፍትሄ ሊሆኑ ከሚችሉ ምክረ ሀሳቦች ጋር በተለያዩ ጊዜዎች አውጥቷል አሁንም በማውጣት ላይ ይገኛል። ነገር ግን ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ ለችግሮች በቂ ትኩረት ተሰጥቶ ዘላቂ መፍትሄ ባለመቅረቡ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች አሁንም ቀጥለው ይገኛሉ፡፡

## የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በሚመለከት የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ የሰሜኑን የትጥቅ ግጭት አስመልክቶ በተደጋጋሚ መግለጫዎችን በማውጣት ትኩረት የሚሹ ሰብዓዊ መብቶች ሁኔታን በመለየት ምክረ ሃሳቦችን ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡ ይህ የትጥቅ ግጭት አሁንም የቀጠለ ሲሆን ግጭቱን ተከትሎ በርካታ ሰዎች ከቤት ንብረታቸው እየተፈናቀሉ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጉዳይ የመንግስት ሀላፊነት የሆነው ለተፈናቃዮች ሰብዓዊ ድጋፍን ማድረስ ይህ ካልተቻለ ደግሞ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች እና ዓለም አቀፍ ለሆኑ ሰብዓዊ አርዳታ ለሚሰጡ አካለት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ናቸው፡፡

ስለሆነም በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል እየተካሄደ ያለውን የትጥቅ ግጭት በመሸሽ በተለየዩ የሀገሪቱ ክፍል ውስጥ በዋናነት በትግራይ፣ በአፋር እና በአማራ ክልል የሚገኙ ተፈናቃዮች፣ ከትግራይ ክልል የመጡ በተለያዩ የአማራ እና የአፋር ክልል ውስጥ የሚገኙ ተፈናቃዮች እና የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ ቀውስ ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች በመንግስት በኩል እየተደረገ ያለው ሰብዓዊ ድጋፍ (ምግብ፣ መድሃኒት እና መጠለያ በዋናነት) በቂ ባለመሆኑ ያለምንም አድልዎ ሰብዓዊ እርዳታን መንግስት እንዲያቀርብ እና በዚህ ረገድ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች እና ዓለም አቀፍ ለሆኑ ሰብዓዊ እርዳታን ለሚያቀርቡ ድርጅቶች መንግስት ችግሮች ከቁጥጥር ውጪ ከመሆናቸው በፊት በአፋጣኝ ሁኔታዎችን እንዲያመቻች ኢሰመጉ ያሳስባል፡፡

## የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተናን በሚመለከት ያሉ ጥያቄዎች፡

የ2013 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤት ከተገለጸበት ጊዜ ጀምሮ ሰፊ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ውጤታቸው አንደገና እንዲፈተሸላቸው ለሚመለከተው አካል ጥያቄ እያቀረቡ በመሆኑ የሚመለከተው ክፍል የተማሪዎችን ጥያቄ በመመርመር አፋጣኝ መፍትሔ እንዲሰጣቸው ኢሰመጉ ያሳስባል፡፡ በጉዳዩ ዙሪያ ከተለያዩ አካላቶች የሚሰነዘሩ ሀሳቦች ማህበረሰቡን ግራ እያጋቡ እና የተማሪዎችንም ስነልቦና እየጎዱ በመሆናቸው የሚመለከተው አካል ተገቢውን ማብራሪያ እንዲሰጥ እና የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

## የኢሰመጉ ጥሪ፡

- የፌደራል እና የሚመለከታቸው የክልል መንግስቶች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በዋናነት በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በታጣቂዎች እየተፈጸሙ ያሉ ጥቃቶችን በአፋጣኝ እንዲያስቆሙ እንዲሁም የዜጎችን በህይወት የመኖር እና የአካል ደህንነት መብቶችን እንዲያስከብሩ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፣

- የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን አስመልክቶ ከመንግስት በኩል የሚሰጡ ሰብዓዊ ድጋፎች በቂ ባለመሆናቸው ነገሮች ከቁጥጥር ውጪ ከመሆናቸው በፊት መንግስት ያለምንም አድልዎ በቂ የሆኑ ሰብዓዊ ድጋፎችን እንዲያቀርብ እና ማቅረብ ባልተቻለበት ወቅት መንግስታዊ ላልሆኑ ድረጅቶች እና ለዓለም አቀፍ የሰብዓዊ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ሁኔታዎን እንዲያመቻች ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፣

- በደቡብ ክልል አማሮ ልዩ ወረዳ እና ኮንሶ ዞን ባሉ አንዳንድ ወረዳዎች ውስጥ ያሉትን የሰብዓዊ መብት ሁኔታዎች የሚመለከታቸው የፌደራል እንዲሁም የደቡብ ክልል መንግስት አካላት በበቂ ሁኔታ እንዲከታተሉ እና በአካባቢው በተደጋጋሚ እየተፈጠሩ ላሉ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄን እንዲሰጡ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፣

- በመጨረሻም መንግስት፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ ሲቪል ማህበራት እና ሰብዓዊነት የሚመለከተው ሁሉ ከላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ የበኩላቸውን እንዲወጡ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ